በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጠቅላይ ፍ/ቤት
የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት
Supreme Court Federal Courts Execution Directorate

በፍርድ አፈፃፀም የሀራጅ ሽያጭ ተሳታፊዎች በሙሉ፣

ጉዳዩ :- ስለሀራጅ ሂደት ግልጽነትና አሳታፊነትን ስለማሳወቅ፣

በርካታ ዜጎች በፍርድ አፈፃፀም የሚሸጡ ንብረቶችን (ቤት፣ተሸከርካሪ፣ማሽን፣የቤት ዕቃ፣የመሳሰሉትን) ከፍርድ አፈጻጸም የሀራጅ ሽያጭ ግብይት መግዛት ይፈልጋሉ።ነገር ግን የግብይት ፈላጊዎቹ የሐራጅ ሂደቱ በውል ባለመረዳት የተነሳ ተጠቃሚ ሊሆኑ እንዳልቻሉ መገንዘብ ችለናል።አንዳንዶቹም ሂደቱን በውል ባለረዳት *የጨረታ ሰነድ የሚሸጠው ዮት ነው* ብለው ቢሮ ድረስ የሚያነጋግሩ ያሉ ሲሆን እንዳንዶች ደግሞ በደላሎች ምክንያት መግዛት አንችልም በማለት ተስፋ የቆረጡ ሰዎች እንዳሉ ተገንዝበናል።በመሆንም ማንኛውም ሰው ለራሱና ለቤተሰቡ አገልግሎት የሚውል ንብረት ከዚህ በታች የተመለከተውን አሟልቶ በመቅረብ መግዛት የሚችል ሲሆን የገዙትን ንብረት መልሰው በትርፍ የሚሸጡና በንግድ ስራ የተሰማሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ደግሞ አስፈላጊውን የነጋዴነት መመዘኛ በሟሟላት የሚከተለውን ሁኔታ በመከታተል የሀራጅ ግብይት ተጠቃሚ መሆን የምትችሉ መሆና ችሁን እንገልጻለን።

1. መግዛት የፈለጉትን ንብረት ከጋዜጣ ማስታወቂያ ወይም ከ7 615 በላይ ተከታይ ባለው የቴሌግራም ቻናላችንን ሳብስክራይብ በማድረግ በየወሩ የሚለጠፈውን የንብረት ዝርዝር አይተው የሚፈልጉትን ንብረት ይምረጡ፤ ቴሌግራም ሊንካችን @ffced ሰርች በማድግ ጆይን ያድርጉ፣
2. ለመግዛት የመረጡንትን ንብረቱን በተመለከተ ከሽያጭ ቀን በፊት 4 ወይም 3 ቀን ቀደም ብሎ ጉብኝነት ሰለሚደረግ በፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት 9ኛ ፎቅ ባለው የጨረታ አዳራሽ ተገኝተው ስለንብረቱ የሚሰጠውን ገለጻ ይከታተሉ ንብረቱ ወደ አለበት ቦታ ሄደውም ጉብኝት ያድርጉ
3. ለመግዛት የመረጡትን የንብረት መነሻ ዋጋ ¼ኛ (cpu) አስርተው በሀራጅ ለመወዳደር ይዘጋጁ፤የንብረቱ ግምት 1/4ኛ መብለጥም ሆነ ማነስ ስለሌበት CPU ተጠንቅቀው ያሰሩ፣
4. በጨረታ ቀን አስፈላጊውን ሁሉ አሟልተው (መታወቂያ፣cpu የመሳሰሉትን) በመያዝ በሀራጅ ጨረታ አዳራሽ በመገኘት ይወዳደሩ፤
5. ስለጨረታ ሂደት አሰራር ግልጸኝነት በተመለከተ የፍርድ አፈጻጸም የመረጃ ዴስክ ሰራተኛውን በማነጋገር ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።
6. የጨረታው አሸናፊ ከሆኑ የንብረቱን ሙሉ ክፍያ በ15 ቀን ለመክፈል ገንዘብ ማዘጋጀትዎን እንዳይረሱ፣

መልካም እድል

የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት

